# አቶ እያሱ ፤ ከድጡ ወደ ማጡ

ከብርሃኑ ሃሰን (9 ጀንዋር 2015)

"አስገራሚ ያልጋ /የመኝታ ጓደኞች ፤ ይሳያስ አፈወርቅ እያሱ አለማየሁን ሲያሽኮረምም" በሚል አረእስት በ 24/01/2015 የተጻፈ የእንግሊዚኛ ጽሑፍ ከአንድ ድረገጽ አገኘሁ ። የጽሑፉን ፍሬ ነገር ለማግኘት ጓጉቼ ስለነበረ ደጋግሜ አነበብኩት ። ጽሑፉ -የአቶ ይሳያስ የፖለቲካ አማካሪ በሆኑት በአቶ ይማነ ገብረአብ አቀራራቢነት አቶ እያሱና አቶ ይሳያስ በሚቀጥሉት ነጥቦች ላይ እንዳስማሙዋቸው ያወሳል ፤

ሀ) አቶ እያሱ - በቀይ ባህር በር ወይም ወደብ መጠቀም ህጋዊና ታሪካዊ መብታችን ነው በማለት በተለይም አሰብን ለማስመለስ የሚታገሉት ተቃዋሚዮችን አቋም ለማስቀየር ፤ የዚህ ዓይነት ጥያቄ እንዳያነሱ ዝም ለማሰኘት

ለ) በምትኩ አቶ ይሳያስ ለአቶ እያሱ ፓርቲ ለ(EPRP) ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፍ የሳይተላይት ቴለቭዥን መርሃግብር (Satellite TV program) ሊፈቅዱላቸውና ውጪንም ሊሸፍኑላቸው ። አቶ እያሱ ይህንን ለማድረግ የተገደዱበት ምክንያት ፤

1. አቶ እያሱ የሚመሩትን ኢ ሕ አ ፓ ለበርካታ ዓመታት-በአገር ቤትም ሆነ ከአገር ውጭ ከተደረጉት የተቃዋሚዮች የፖለቲካ እንቅስቃሴ የተሜውተው ሚና ስላነበረ ፤ ርቆ ተቀምጦ ስለነበረ
2. ፓርቲያቸው ኢ ሕ አ ፓ በአሉታ/በኔጌቲቭ እንዲፈርጅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ተብለው ስለተከሰሱ/በመከሰሳቸው
3. በአመራር ብቃታቸው ባለመደሰት የተነሱ የወስጥ /የአባላት ተቃውሞ ስለገጠማቸው

4 ከእላይ በ (ለ) የተጠቀሰውን የዜና ስርጭት አወታር/ ሚዲያ ማግኘት ፤ ከላይ የተጠቀሱትን ወቀሳዎች እከስበታለሁ፤ አለሁ ለማለትና በሕዝብ ዘንድ ያጡትን ፖለቲካዊ ዋጋና ገጽታ ያድስልኛል የሚል እምነት ስላላቸው ነው ይላል ጽሑፉ ።

- ይህ የተባልው ስመምነት እውነት ከሆነ - ባትወክሉኝም እኔ ኢ ሕ አ ፓን ወክዬ የኤርትራን ብሄራዊ ሉዓላዊነት ከተቀበልኩ ፤ አሚን ካልኩ ፤ ካጸደኩ ወዘተርፍ -- የትኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት በኤርትራና በቀይ ባህር በር ወይም ወደብ ላይ የአለኝታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ ማንሳት አይችልም ማለታቸው አይደለምን ? ይህ ማለት በጸረ ኢትዮጵያ ግዛት አንድነት መቆም አይደለምን ? ይህ ማለት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዮችና የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ በጣም መናቅ አይሆንምን ? ታዲያ በምን መልኩ ነው ከዚህ አንቀጽ ከፍ ብሎ ከአንድ እስከ አራት የተነጠቡትን ጥፋቶቻቸውን የሚያካክሱት ወይም የሚያጣፉት ? ከድጡ ወደ ማጡ እየተዘፈቁ !

- ያለአባላት የፖለተካ ፓርቲ ፤ያለአባላት ድርጅት ፤ ያለማህበርተኛ ማኅበር ወዘተ..ስለማይኖር - አቶ እያሱ ከኢሳያስ ጋር ይህንን መሰል ው

- ሲዋዋሉ ከአባሎቻቸው ጋር ተመካክረው ይሆን ? የኢ ሕ አ ፓ አባላት -ዓላማ ጽኑ ፤ የሰከነ የፖለቲካ ንቃት ያላቸው ፤በሃገራቸው ጥቅምና ሉዓላዊነት ላይ ከማንም የማይደራደሩና፣ አርቀው አሳቢ ስለሆኑ - በዚህ ዓይነት ታሪካቸውን በሚያጎድፍ ድርድር የሚዘፈቁ ያሉ አይመስለኝም ፤ ከሆነም በኢ ሕ አ ፓ ስም አቶ እያሱ ብቻቸውን የተዋዋሉት ውል ይሆናል ።

- አቶ እያሱ ባለፉት ከአምስት እስከ ሰባት ዓመታት- በባዕዳን አገራት ያሉትን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ጸረ ወያኔ አንድንት ለመፍጠር ይደረጉ የነበሩትን ጥሪዮችና ጥረቶች ሲቃወሙ የቆዩ ሰው ናቸው ። ለመቃወማቸው ሲሰጡ የነበሩትን ምክንያቶች ፤ (1) የህብረት ትግል ከዚህ ቀደም ሞከረነው ስለአልሰራ አያስፈልግም (2) የሚያዋጣው ሕዝባዊ አመጽ ነው -ግብታዊ ሕዝባዊ አመጽ ያለመሪ ድርጅት ማለታቸው ይመስላል - ግልጽ አያደርጉትም (3) ኑ ተሰባስበን እውነተኛ ህብረት እንፍጠር -አሁን ያሉትን ተቃዋሚዮች ወደጎን ተትው - ለሃሳባዊ ሃቀኛች ህብረት ጥሪ ማቅረብ -በማን አሰባሳቢነት ፤ እንዴት ፤ መቼ ፤የት መሆን እንዳለበት አይገልጹትም ። አሳባቸው

ተሰንጥቆ ሲገመገም - ፒያሳ ወይም አራት ኪሎ ወይም ሜክሲኮ አደባባ ላይ ተገናኝተን የሃቀኛ ተቃዋሚዮች ህብረት እንፍጠር የሚሉ ይመስላል ።

- አቶ እያሱ አስመራ ተቀምጬ ወያኔን እታገላለሁ ፤ በሳተላይት ቲቪ ጽረ ወያኔ ፕሮፓጋንዳ አደርጋለሁ ፤ የወያኔ የሥልጣን ዘመን አሳጥራለሁ ፤ ስለሆነም በቀይ ባህር ወደብም ሆነ በኤርትራ ነጻ አገራዊነት ላይ አንዳችም ጥያቄ አታንሱ ይሉናል ። "አስገራሚ ያልጋ/የመኝታ ጓደኛሞች........." በሚል አርእስት የተጻፈውን የእንግሊዝኛ ጽሁፍ/አርቲክል አግኝተው የአነበቡ ኢትዮጵያውያን አስተያየት የሚያመዝነው -የአቶ እያሱ ወደ አስመራ መሄድ ' ወያኔና ሻቢያን የበለጠ ለማቀራረብ ፤ ወዳጅነታቸውን አጠናክረውና ተጋግዘው በትረመንግሥታቸውን ላይ እንዲቆዩ ለመምከር ይሆናል እንጂ ጸረ ወያኔ የፖልቲካ ሚና ለመጫወት አይደለም ይላሉ ። ኢ ሕ አ ፓን ማዳከማቸውን ፣ የተቃዋሚዮች ህብረት እንዳይሰምር አስተዋጽዖ ማድረጋቸውን ፣ መጽሐፋቸውን በወያኔ ባለሥልጣኖች ማስመረቃቸውንና ለኤርትራ ብሄራዊ ነጻነት መቆማቸውን በማዘመድ -አንዳንድ ጠጣር ተጠራጣሪዮች(skeptists) - አቶ እያሱ 'ኢ ሕ አ ፓን /EPRP እየመሩ- የወያኔም የሻቢያም ወኪል ነበሩ' ይላሉ ።

- ለዚህ ጽሐፍ ምን ዓይነት አርእስት ልስጠው በማለት እነኚሁ እስኬፐቲክስ (skeptists) ጠየኳቸው ፤ እስቲ አንተ ልትለው የፈለከውን ንገረን ! አሉኝ ፤ የአቋም መንሸራተት ፣ የፖለቲካ ቀውስ ፣ ግራመጋባት ፣ ማታለል (sophism) ፣ ከድጡ ወደ ማጡ አልኳቸው ፤ የመጨረሻውን አርእስት ቢሆን ይመረጣ
- ! አሉኝ ። ለምን ? 'ከድጡ ወደ ማጡ' - "ከትንሽ ችግር ወደ የከፋ ችግር ፣ ከትንሽ ቀውስ ወደ ባሰ ቀወስ ፣ ከቀላል ስህተት ወደ ውስብስብ ስህተት ወዘተርፈ መዜፈቅ ማለት ስለሆነ" በማለት ምክራቸውን ለገሱኝ ። እኔም እጅግ በጣም አመሰግናለሁ ! ብዬ ተቀበልኩት ።